# አሸባሪዎች መሆናቸውን እናምናለን ከጎናቸውም እንቆማለን

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

*ጀግናዋ ሰርክአለም እንዲህ አለች "…. ስማቸው ያልተነገረ ብዙ እስክንድሮች ታስረዋል። አንድ እስክንድር ሲታሰር አንድ ሺህ እስክንድሮች ይመጣሉ። የእያንዳንዳችን በር አስኪንኳኳ መጠበቅ ግን ሽንፈትን መቀበል ነው …."*

*ባለቅኔዋ ጂጂም እንዲህ ተቀኘች ….. ወያኔ ያገሬውን ደምና ስጋ ለብሶ በጠላት እስትንፋስ የተከሰተ እርኩስ መንፈስ ነው ትለዋለች*

*"… ያልሰማነው ነገር ያላወቅነው መጥቶ*
*ባዕድማ ቢሆን ወግ ነበረ ከቶ….."*
*"……በቃኝ አትልም ወይ ብቅት ብሎ ይብቃ፣*
*እንዲህ ያለው ኑሮ ሀዘን ነው ሰቆቃ። .."*

*በፍጥረት ሕግ ሴት በቃ ብላ ከተነሳች ግንባሩን የሚያጥፍ ወንድ የለም። ሴት የእንበለዘር ሰብሳቢና ተኪ ናት ተንከባካቢና አሳዳጊም ናት። ታላቅ የተፈጥሮ ሸክም በጫንቃዋ ላይ ሰፍሯል። እናም ጀግኖች እህቶቻችን አደጋውን አይተውታል ለመጋፈጥም ቆርጠዋል። ሸብሬ ለዚህ ሞተች፣ ብርትኳን ለዚህ ታሰረች። ሰርክአለም በእስርቤት ወንድ ልጅ ወለደች፣ ርዕዮትም እስር ቤት ነች…… አይበቃችሁም ወይ እያሉን ነው። ወግ መጠረቅ ይብቃና ውጤት ወደሚያመጣው የነፃነት ትግል እንቀላቀል እያሉን ነው። ወንድ ሴት ሕፃን አዛውንት ሳይባል ለነፃነት መስዋዕት ሆነዋል። መስሚያ ጆሮ ማሰቢያ አእምሮ ያለን በሙሉ ለነፃነትና ለሰብዐዊ ክብር እንነሳ!!!*

ሽብር ማለት ልዩ ትርጉም ካልተሰጠው በቀር የፍርሃት ከፍተኛው ደረጃ ነው። የሽብር መንስዔው ደግሞ ገዢዎች በፈቀዱትና በለመዱት መንገድ ሕዝብን ቀጥቅጠው አንደበቱን ዘግተው መግዛት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱና የሚይዙት የሚጨብጡት ሲጠፋቸው የሚይዛቸው ብርክ ነው። መገለጫውም በሀገርና በሕዝብ ላይ የሚወስዱት የጥፋት እርምጃ ነው። በዚህ የነሲብ እርምጃቸው ይበልጥ እየተወገዙ፣ ሚሊየኖች የትግል ጎራውን እንዲቀላቀሉ ስለሚያደርጉ የእድሜያቸውን ማጠር ያቀርቡታል። መቅበዝበዝና መለማመጥ፣ መግለጫና አዋጅ ማስነገር ያበዛሉ። ደርሶ የአገር አሳቢና ተቆርቋሪ መምሰልን ይሻሉ። እድሜ ያረዝምላቸው ይመስል አጠገባቸው ያሉትን ከስልጣን ያስወግዳሉ። ለመፅዳት በሞከሩ መጠን ይጨቀያሉ። የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት መራሹ ኢሕአዴግ መሸበሩ ይገባናል። ፈራሁ ቢልም አይደንቀንም። እንቅልፍ አጣሁ ቢልም እውነት ነው።

በቅርቡ ኩሩና ቆፍጣና ገፅታውን እያሳየ  ሙባረክም አሸባሪዎች ናቸው ብሎ ነበር። በቃሬዛ ፍርድ ቤት ሲቀርብ ግን ግርማ ሞገሱ ሁሉ ጠፍቷል። መሸበሩ ግልፅ ነበር አሸባሪው ደግሞ የግብፅ ሕዝብ ነው። ጋዳፊም አረንጓዴውን ማኒፌስቶ እያውለበለበ አትነሱም ወይ ብሏል ወደ ጎሳዎቹ እየተመለከተ። የኑክሌር ጥቃት የሚቋቋም ከምድር በታች የተሰራ ቤትም ገንብቶ ነበር። መደበቂያ ግን አልሆነውም። አሸባሪው ደግሞ የሊቢያ ሕዝብ ነው።  የየመኑም የሶርያውም ያንኑ ነው የሚሉት ግን የሚቋቋሙት የሕዝብ ቁጣ አይደለም ከፊታቸው የተገጠገጠው። እናም ተሸብረዋል።

የሚገርመው ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውም እንኳ ሀገራቸውን ለማፍረስ የተነሱ አልነበሩም። እብሪት እንጂ አገር አሳልፎ የመሸጥ እኩይ ባህርይ አልተጠናወታቸውም። ሕዝባቸውን በጉልበት ማስተዳደር እንጂ እንደ መለስ በሀገር ጥላቻ የሰከሩ አይደሉም። እንደ ባዕድ ገዢና እንደ ወራሪ ጠላት የተማረውን እያጠፉ ትውልድን ወደ ጭለማ እየጨመሩ ባልተገራ አንደበት ባለሀገሩን እያዋረዱ ጥቅሙን ለባዕድ እየሸጡ የገዙ አልነበሩም። ወያኔ ግን ከማንም በላይ በጥፋቱ ሰልጥኖበታል። ታድያ ወያኔን ማሸበር የፅድቅ እንጂ የኩነኔ መንገድ ሊሆን እንዴት ይቻለዋል? ራቁቱን የቆመ እውነት ሰይፍና ጎራዴም ሳይመዘዝ፣ ጠመንጃና ታንክም ሳይሰለፍ የማሸበር አቅም አለው። ይህንንም ብዙ የሀገሪቱ ጀግኖች አረጋግጠውታል። ዛሬም የምንመለከተው ከዚህ የተለየ አይደለም።

በሰላ አንደበታቸውና በትንታግ ብዕራቸው ሰላምና መረጋጋቴን ነፈጉኝ በዱር በገደል ዘምቼ በጠመንጃ አፈሙዝ ከያዝኩት ስልጣኔ ለመፈንገል በአደባባይ እየሞገቱ እንቅልፍ ነሱኝ በማለት የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት መራሹ ኢሕአዴግ አሸባሪዎቹን ማገቱን ቀጥሏል።

በርግጥም እነኚህ ወያኔ አሸባሪዎች መታሰር፣ መታገዝና ከስራ መገለል ያልበገራቸው በመሆናቸውና ሞትንም ፊትለፊት ለመጋፈጥ ከወያኔ ጉያ ሆነው መታገላቸው እጅግ አደገኛ መሆናቸውን ያስመሰክራል። እስክንድር ነጋና አንዱአለም አራጌ አሸባሪዎች ከሆኑ እኛም ቀንደኛ አሸባሪዎች ልንሆን ይገባናል። ርዕዮት አለሙ በዚህ ከተፈረጀች የህገሬ ጀግና ሴቶች ሁሉ ለወያኔ በእርግጥም አሸባሪ ናቸው። ውብሸት ታዬ በሽብር ወንጀል ከተከሰሰ የተገፋው ወጣት ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንደዚያው ነው። ደበበ እሸቱ አሸባሪ ከሆነ በሀገሪቱ ያሉ ስመጥሩ አዛውንቶች ሁሉ አሸባሪዎች ናቸው። እየኮራንባቸው ከጎናቸው የምንቆም ኢትዮጵያውያን በሙሉ ክፋትን፣ ጥላቻን፣ ዘረኝነትንና ሙስናን በማስፋፋት ሀገር የሚያፈርሱትን ሁሉ ለማሸበር ብቻ ሳይሆን ለማሸነፍም የቆረጥን መሆን አለብን።

በቅርቡ የአንድነት አመራሮች የሰጡት መግለጫ ልባችንን የሚያሞቅ፣ ሞራላችንን የሚያድስና ለበለጠ ትግል የሚያነሳሳ ነው። ተገፋን! ሰለቸን! በቃን!! ክፋታችሁ አፍንጫችን ላይ ደረሰ! ከዚህ በላይ ወርደት፣ ከዚህ በላይ ጥቃት የለም ማለታቸው እውነት ነው። እነርሱ አሸባሪዎች ከሆኑ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአሸባሪነት ለመመደብ ዝግጁ ልንሆን ይገባል።

እውነትን ማሰር አይቻልም እንደተባለው ሁሉ ክፋታቸውን የሚያሳያቸው ቅዠት መኝታ ቤታቸው ድረስ ይመጣል። የገነቡት ሕንፃ በሰላም የሚተኙበት አይደለም።  የዘረፉት ገንዘብም ምቾት አይሰጣቸውም። ያጠፉት ነብስ ልባቸውን ይቧጥጣቸዋል። ያሰለፉት ሰራዊትም ይከዳቸዋል። ለሆዱ የሚያድር ሁሉ ትናንት ያበላውን ወያኔ ትቶ ለነገ ፍርፋሪ ወደሚያገኝበት ሲሮጥ ወያኔዎች ብቻቸውን ይቀራሉ። በዚህ መርበትበት ሳቢያ እውነትን ከአንደበታቸው ያወጡ ሁሉ ሊታሰሩ ይችላሉ እውነት ግን አይታገትም ማንም ሊያስረውም አይቻለውም። ክፋታችሁ ከምንሸከመው በላይ ሆነ ከትከሻችን ውረዱልን ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚለው።  እኛ ስንነሳ ጥቅማቸውን ለማስከበር ከጎናችሁ የቆሙ ፈረንጆችም ሰልፋቸውን ማሳመራቸው አይቀርም። ትናንት ከትናንት ወዲያ የታዘብነው ይህንን ነው። የናንት ዕጣ ደግሞ የከፋ ነው። ሕዝቡን ጠልቶ ባዕድን ተማምኖ በስልጣን መዝለቅ ከቶውንም አይቻልም። ስለዚህ የነፃነት ታጋዮቻችን አፋኞችን አሸባሪ እንደሆኑ እናምናለን ከጎናቸውም እንቆማለን።

ክበር ለኢትዮጵያዊነት፣ ክብር ለኢትዮጵያ ጀግኖች ይሁን!!

biyadegelgne@hotmail.com